# ትውስታ - ወቴዲ-ብርቱካን. . .

# ለእልፍ-አዕላፍ ግፉዓን!

ለቴዲ• ለብርቱ

በሽፍጥ፣ በተንኮል፣ በቂም.. ተበክለው፣
በጥላቻ፣ በሃኬት፣ በበቀል.. ተሞልተው፣
እልፍ-አዕላፍ ፍቅር መሸከም አቅቷቸው፣
ያገሬን ሰው ፈጅት አቤት! ጭካኔያቸው::

. . . . . . . . . . . . .

ተፈጥሮ ቀምማ - በቸረችው ጥበብ፣
«ነፍስ» ሊዘራበት - ተስፋ ያጣውን ሕዝብ፣
ቅኔውን አሳክቶ - ሙዚቃ ቀምሮ፣
በየሰዉ ልብ ውስጥ - እምነቱን አኑሮ..፤
ጀግኖች ባወደሰ - ላገር የሠሩትን፣
ዕርቅን በሰበከ - ይቅር ባይነትን፣
ለታሪክ፣ ለውበት፣- ላንድነት፣ ለፍቅር. . .፣
ደጋግሞ ባዜመ - ለአገሩ ክብር፣
ከፍ አርጎ ውብ ድምጹን - «ኢትዮጵያዬ» ባለ፣
በሽረኞች ሴራ - ከወህኒ ተጣለ::




እልፍ-አዕላፍ ፍቅር መሸከም ተስኗቸው፣
ጥላቻን መረጡ አቤት ክፋታቸው!
ትውስታ! ለቴዲ - ላገር-ወገን አጋር፤
እናስብሃለን! ለውለታህ ክብር!

. . . . . . . . . . .

በቅን ስነምግባር - ተኮትኩታ አድጋ፣
ንቢት ተሰማርታ - እውቀትን ፍለጋ፣
ከተፈጥሮዋ ጋር - የሚጣመር እውነት፣
ፍትህን ሽመተች - ለሰው ልጅ ነጻነት..፤

የቀሰመችውን - የፍትህ አበባ፣
የቀጠፈችውን - የሰላም ዘንባባ፣
ለውጤት ለማብቃት - ቀፎ ስትገነባ፣
ከማሩ ወለላ - እንዲቃመስ ሕዝቧ..፣
እባብ ተቆጭቶ - በልቡ ተስቦ፣
ሊያስቀራት አሰበ.. - ካላማዋ ስቦ::



የብርሃን ራዕይ - ለጉዞ ሰንቃ፣
በተስፋ ተምሳሌት - በተነሳች ታጥቃ፤
የእናትነት ባህርይ - መልካም ሰብዕና፣
የርህራሄ ምንጭ - የሕዝብ አምሳል መሆኗ፣
ለሰላም፣ ለፍትህ. . . በቁርጥ መሟገቷ፣
«ጠላቶቿን» ልቃ - ሃቅ አልክድ ማለቷ...፣
ይህ ነበር «ጥፋቷ»!
ቃሏን ያከበረች - ውብ ኢትዮጵያዊቷ!

# ለእልፍ አዕላፍ ግፉዓን

በሽር የታጀለ፣ ብርሃን ያልታደለ፣ ግብረ-አራዊት ብካይ፣
ጨለማ ቤት ዘጋት - የሰው ልጅ እንዳታይ፣
እልፍ-አዕላፍ ሰላም - መሸከም ተስኖት፣
ብቀላን መረጠ - የክፋቱ ክፋት!
ትውስታ! ለብርቱ - የትውልዱ መሪ፣
እናስብሻለን!   ሕያው ቃል አክባሪ!!

. . . . . . . . . . . . .




በግላጭ ተገፎ - ሰብዓዊ መብታቸው፣
በንቀት በትቢት - የተተፋባቸው፣
ሽጉጥ ባናታቸው - ተደቅኖባቸው...፣
በጠመንጃ ሰደፍ - ተወግሮ ሽንጣቸው..፣
ባገር ፍቅር እምነት ጽናት በተመኩ፣
በሥነ-ልቦና - ሽብር የታወኩ፣
ስንቶቹ . . . ስንቶቹ . . . መዝገብ ያላያቸው፣
ሥም ያልወጣላቸው፣ ቤት እሚቆጥራቸው::

እንዳይላወሱ - ባገራቸው ምድር፣
ባዋጅ ተደንግጎ - ስቃይ የቁም እስር...፣
ተበይኖባቸው - ሰቆቃ እሚኖሩ፣
ስንትና ስንት ሺ . . . በእልፍ የሚቆጠሩ::

...በአርሲ ተራራ፣ በበደኖ ገደል፣ ባዋሳ ሲዳሞ..፣
በአምቦ ሜዳ፣ በኦጋዴን በረሃ..፣
በጋምቤላ ጫካ፣ በወላይታ ጋሞ..፣
በመቱ፣ በባሌ፣ በጅማ፣ ወለጋ...
በጎጃም፣ በጎንደር፣ በወሎ፣ በሸዋ...
ኡርሶ፣ ሸዋሮቢት፣ ደዴሣ፣ ሰንዳፋ...
ፍቼ፣ ቃሊቲ፣ ሐረር፣ አዲስ አባ. . .፣
በትግራይም ጉድጓድ ጨለማ ውስጥ ታስረው...፣
እንደ ዶሮ ጥሬ እሚጣልላቸው...፣
በስቃይ ያሉትም በስቃይ ያለፉ..፣
ባገራቸው ምድር በግፍ የተገፉ፣
በጭካኔ ጥይት ጭፍጨፋ የረገፉ፣
ስንቶቹ . . . ስንቶቹ . . . እልፍ-አዕላፎቹ፣
እማይዘነጉ የሰላም ጀግኖቹ!!

. . . . . . . . . . . . .



በደልን ጠልታችሁ - ግፍን ተዋግታችሁ፣
ፍትህ፣ ነጻነትን . . . ኢትዮጵያን ብላችሁ፣
ባረመኔው ጥይት - ከቶ የወደቃችሁ፣
ደማችሁ ደመ-ከልብ - ሆኖማ አይቀርም!
ሲታወስ ይኖራል፣ ከትውልደ-ትውልድ...
ህያው ተግባራችሁ በርቶ ለዘልዓለም!!

ጌታቸው አበራ
ሰኔ ፪ሺ፩ ዓ/ም
(ጁን 2009)

---

ሥማቸውና ግብራቸው በይፋ ጎልቶ በታወቀው በቴዲ እና በብርቱካን ሥም፣ በመላ አገሪቱ በየእስር ቤቱና በየማጎሪያ ሥፍራው. . . በአመለካከታቸው ልዩነት ሳቢያ ብቻ፣ ፍትህን ተነፍገው፣ በወያኔ/ኢሕአዴግ የጭካኔ ተግባር ለሚሰቃዩ የአገሬ ልጆች ሁሉ ማስታወሻ ትሁን!!